# በለስ ቀናን

*ከተዘራ ጌታሁን አሰጉ*

በለስ ቀናን ዘንድሮ
ያሰብን ያለምነው ሰምሮ ፤

አባይ ጣና በደቦ
ያገር ልጅነቱን አስምስክሮ ፤

አባይ ጣና ዳር አንበሳ አገሳ
ማነው አይነሳም ያለ ካሳ ፤

አባ ዳኘው አይሳሴው በላይ
ሲፎክር ታየ ጣና አፋፍ ላይ ፤

ንስር ቢወራጭ በለስን ሊያምስ
ሲያምረው ሊደቆስ በመይሳው ክንድ ፤

በለስ ጎመራ አበራ አማረ
መቸ ቀረ ለማይወግነው እንደገበረ ፤

አባይ አባይ አባይ
ትላንት ነበርክ ለሌላ አዳይ ፤

ለካስ ማበይህ
እቡይ ንፉግ መሆንህ ፤

ከፍቶህ ነበረ ቅር ብሎህ
መነታረክ መፋተጋችን አስከፍቶህ ፤

መወለድህ መፈጠርህ ከኛ ሆኖ
ለባእድ ማዳላትህ አይሎ ፤

ውስጠ ሚስጥሩ ለልጆችህ ተሰውሮ
ፈዋሽ ወጌሻ ሐኪም ሳይገኝለት ኖሮ ፤

ራስህ ሆንክ ፍቱን ፈዋሽ
የጥማታችን ድርቀት አራሽ ፤

መፋተጉን መናረቱን ስናርቅ
የፍጡራን ያንተም ምንጭ መሆናችንን  ስናውቅ ፤

ፊታችን ወደአምላክ አቀናን
እሱም ሰማን አንተም ቀና አልክ ፤

ንፍግናውን ወደዝያ አልክ
ልጆችህን በእንባ ሳይሆን ፤

በበረከትህ አሰነይክ
ችርነትህን አበዛህ ፤

ፊትህ ወደኛ ዞረ
በብርሃንህ ፊታችን አማረ ፤

ማሲንቆየ የግጥሜ ስንኝ
አንተን ያቆላብስ ያመስግን ፤

አባይ ከበር ተመስገን
የኢትዮጵያ ልጆች ብርሃን ፤

ይቅር አልከን
ተሰንየህ አሰነይከን ፤

የልጆችህ ማረር መበገን
ግራ መጋባት መቆጭት ፤

እንቆቅልሹ ድሩ ተፈታልን
አዚሙ ደንቀራው በጸበልህ ታጠበልን ፤

ትላንት ንዴቱ ያስለቀሰን
በቁጭት አንገታችን የደፋን ፤

ውዳሴ ቅኒያች ፋከራ ትችት ነበረ
ዛሬ መወድስ ቃላችን ተቀየረ ፤

አባይ አደላ ለሰጋው ወገነ
ጎሽ አንበሳየ ያገር መኩሪያ ከለላየ ፤

ከእንግዲህ ቃል ገባን ላንኮንንህ
በክፉ ላናነሳህ ላናማህ ፤

እልቅስዋችን ታቀበ
በደስታ ተቀየረ ተዘየረ ፤

ያንተን መከፋት ላሰቡ
እጅህን አመድ አፋሽ ላረጉ ፤

ከወገነህ ሊለዩህ ለዶለቱ
ከአባሻ ጋር ሊያቃቅሩህ ላሰቡ ፤

እንደወራጅ ውሃህ እንደጅረትህ
ተነሳን ልንቆም ከጎንህ ፤

አይዞህ ብለህ ጸጋህን ጀባ ስትል
ማን ሞኝ አለ ያንተን ክፉ የሚያርይ ፤

ልናሞግስህ አደራህን ልንመልስ
ከዳርቻህ ዘብ ቆምን ልንጠብቅህ ፤

ውሃህን ሳትሳሳ ስትለገስን
አጥንታችን ታጠረ ከለላ ሊሆንልህ ፤

ላንተም ለኛም ሰንክ ሊሆን ላቅማማ
ብለህ ንገረው የአምናው የትናቱ በቃ

ወገን ከወገኑ ተጋመደ
በለው እኛም ነቃን ታረቅነ ፤

በቃ አበቃ መተቱ ተፈታ ፎረሸ
የአባይ እና የለጆቹ አንድነት አገረሸ።

*ከተዘራ ጌታሁን አሰጉ/ ከምድረ ለንደን/*